# ማስታወቂያ ለሰራተኞች

## ከጁላይ 2020 ጀምሮ የሚቀርብ አዲስ ጥቅማ ጥቅም

### በኮሉምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የቤተሰብ ፈቃድን የሚመለከት መረጃ

አሰሪው ለኮሉምቢያ ዲስትሪክት ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የቤተሰብ ፈቃድ ሕግ የሚገዛ ሲሆን፣ ይህ ሕግ ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች መስፈርቱን ለሚያሟሉ የወላጅ፣ የቤተሰብና የሕክምና ዝግጅቶች ከደመወዝ ጋር እረፍት እንዲወጡ ይፈቅዳል። ከደመወዝ ጋር የሚሰጥ የቤተሰብ ፈቃድን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ከደመወዝ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ጽ/ቤት ድረ ገጽን በ dcpaidfamilyleave.dc.gov ላይ ይጎብኙ።

## ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች

ከደመወዝ ጋር በሚሰጥ የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም ስር የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ ሽፋን የሚሰጠው ሁኔታ ከማጋጠሙ በ ዲሲ ውስጥ ለሚገኝ አሰሪ የሚሠሩ መሆን አለብዎት። አሰሪዎ ደመወዝዎን ለስራ ቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ ማሳወቅና ለእርስዎ በሚከፈለዎት ደመወዝ ላይ ተመስርቶ ግብር መክፈል አለበት። ሽፋን ያለዎት ሰራተኛ መሆንዎትን ለማወቅ፣ አሰሪዎን መጠየቅ ወይም ከታች ባለው አድራሻ ከደመወዝ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ጽ/ቤትን ያነጋግሩ። ደመወዝ በሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም የሚሸፈኑ ከሆነ አሰሪዎ ሊያሳውቅዎ ይገባል። አሰሪዎ ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድን በተመለከተ ቢያንስ ሶስት (3) ጊዜ መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል፡-

1. በሚቀጠሩበት ጊዜ (ከጃንዋሪ 2020 በኋላ ከተቀጠሩ)፤
2. ከ 2020 ጀምሮ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ፤ እና
3. (በ 2020 ወይም ከዚያ በኋላ) ደመወዝ በሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም ስር ባሉ ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ የሚካተት ፈቃድ ከአሰሪዎ ከጠየቁ።

## ሽፋን ያላቸው ክስተቶች

ደመወዝ ለሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ የሚሆኑባቸው ሶስት (3) ዓይነተ ክስተቶች አሉ። እያንዳንዱ የፈቃድ ዓይነት የራሱ የብቁነት ደንቦችና በአንድ ዓመት ውስጥ ማግኘት በሚችሉት ጥቅማ ጥቅም የጊዜ ርዝመት ላይ የራሱ ገደቦች አሉት። በአንድ ዓመት ውስጥ የወሰዱት የፈቃድ ዓይነት ምንም ቢሆን፣ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ **8 ሳምንት** በላይ ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት አይችሉም። ጥቅማ ጥቅሞች ሊያገኙ የሚችሉባቸው ሶስት የፈቃድ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የወላጅነት ፈቃድ - አዲስ ከተወለደ ልጅ ጋር ለመላመድ በዓመት እስከ 8 ሳምንት የሚቆይ ጥቅማ ጥቅም ይሰጣል።
2. የቤተሰብ ፈቃድ - የቤተሰብ አባልን ለመንከባከብ የሚሰጥ በዓመት እስከ 6 ሳምንት የሚቆይ ጥቅማ ጥቅም ነው፤ እና
3. የሕክምና ፈቃድ - በራስዎ ላይ ለሚከሰት ከባድ የጤና ችግር በዓመት እስከ 2 ሳምንት ድረስ የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅም ነው።

በዲሲ የቤተሰብ እና የህክምና ፈቃድ ህግ (DCFMLA) መሠረት ለስራ ደህንነትና ጥበቃ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ። ስለ DCFMLA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ድረ ገፅ ይጎብኙ: ohr.dc.gov.

## ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከቻ ማስገባት

የወላጅ፣ የቤተሰብ ወይም የሕክምና ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞች ስር የሚወድቅ ክስተት ካጋጠመዎት ለጥቅማ ጥቅም ስለማመልከት ተጨማሪ መረጃዎችን ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጽ/ቤት ድረ ገጽን በ **dcpaidfamilyleave.dc.gov** ላይ ይጎብኙ።

## የጥቅማ ጥቅም መጠኖች

ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞች የሚመሰረቱት አሰሪዎ ለእርስዎ በከፈለውና ለስራ ቅጥር አገልግሎቶች ሪፖርት ባደረገው የደመወዝ መጠን ላይ ነው። የደመወዝ መጠንዎ በተሳሳተ መልኩ ሪፖርት ተደርጓል የሚል እምነት ካለዎት፣ ስለ ትክክለኛ የደመወዝ መጠንዎ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። ከጁላይ 1/2020 እስከ ኦክቶበር 1/2021 ድረስ ከፍተኛው ሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ $1,000 ነው።

## የሰራተኛ ጥበቃ

ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ፕሮግራም እርስዎ ፈቃድ ሲወጡና ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅም ሲያገኙ ለስራዎ ጥበቃ አያደርግልዎትም። ይሁን እንጂ፣ ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን በመጠየቅዎ ወይም በማግኘትዎ ምክንያት በአሰሪዎ ከሚወሰዱብዎ ጉዳት አድራሽ እርምጃዎች ጥበቃ ሊኖርዎት ይችላል። እነዚህ ጉዳት አድራሽ እርምጃዎች የተወሰዱት ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን በመጠየቅዎ ወይም በማግኘትዎ ምክንያት ከሆነ "የብቀላ ተግባር" ተብለው ይታወቃሉ። የብቀላ እርምጃ ተወስዶብኛል የሚል እምነት ካለዎት፣ ለዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ጽ/ቤት (OHR) ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን፣ ጽ/ቤቱም ቅሬታዎችን የሚቀበለው በቀጣዩ አድራሻ ነው፡- **www.ohr.dc.gov**።

ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ቀጣዩን ደመወዝ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ ጽ/ቤት ድረ ገጽ ይጎብኙ **dcpaidfamilyleave.dc.gov**፣ በ **202-899-3700** ይደውሉ ወይም ወደ **does.opfl@dc.gov** ኢሜይል ያድርጉ።